

**COLONEL KASAYE CHEMDA, is a highly decorated Ethiopian officer who has graduated from Harar Military Academy in Ethiopia (1970), Fort Knox Army Armour School in Kentucky, US (1976) and Viestral Field Academy, USSR (1981). He is godfather and soul of the elite 16TH Senteq Mechanized Brigade.**

# “ምን ሜካናይዝድ? መከራይዝድ እንጂ”

ክፍል ፩

ኃይለ መንገሻ ዑቅበ
ቶሮንቶ፡ ካናዳ
ፌብሩዋሪ 24፡ 2019

## የጦር ሜዳ ውሎዎች ሲቃ ከምስራቅ እስከ ሰሜን ካሳየ ጨመዳ

ኣራተኛ ዕትም
2010 ዓ. ም. (2018 ፈረንጅ ኣቆጣጠር)
ኣዲስ ኣበባ

በቅርብ ግዜ፡ ብርጋዴር ጄነራል ነበር ካሳየ ጨመዳ፡ ኣዲስ ኣበባ በሚገኙ የኢትዮጵያ የብዙሃን መገናኛ ቀርበው፡ ስለ የኤርትራዎች ጀግንነት እንዲህ ብለዋል። **“እውነት! እውነት ልናገር’ና! እነሱን ናቸው እኛን ያሸነፉን?”** ልሳናቸው ሰማነው፡ በኤርትራ መሬት ኣኳያ’ስ ሁኔታው እንዴት ነበር? ቀጥሎ፡ ከብ/ጄ. ነበር ካሳየ ጨመዳ መጽሓፍ፡ ለኣንባቢያን የቀረበ ስናፕ ሾት እንመለከታለን።

ገጽ 167

## ለእልቂት የተደገሰው የመለብሶ ጠላት ጀርባ ግዳጅ

ኣቆርዳት እያለን ጠላት በመለብሶ ግንባር ድንገተኛ ማጥቃት ሰንዝሮ 18ኛ ተራራ ክፍለ-ጦርን የተወሰነ ቦታ ነጠቀው። ያንን መሬት ለማስመለስ እኔ ከጠላት በስተጀርባ በሁለት እግረኛ ሻለቃ እንድገባ ተፈለገ።

በትርጉመ-ቢስ የዊዓ ጉዞ ሠንጥቅን ለኣደጋ ለማጋለጥ እንደተሞከረው የመለብሶው የጀርባ ግዳጅ የማይታሰብ ኣደገኛና መደምሰስንም ሊያስከትል የሚችል ግዳጅ ነበር።

በነጋራችን ላይ ሰንጥቅ እስካሁን ያልተመታ ጦር ነው። ለማነኛውም በቀጥታ ትእዛዙ እንደደረሰኝ ከኣቁርደት ተነስቼ ሓጋዝ ገባሁ። ሓጋዝ ላይ ቴክኒካል ክፍሎቼን ትቼ በእግር ሻለቃዎችን ይዤ በመለብሶ ጀርባ እንድገባ ተደረገ።

የሚያሳዝነው ነገር እኔና ወተሃደራዊ እዙ የምንነጋገርበትን የሬድዮ ኮድ በሙሉ ጠላት መፍታት ይችል ነበር። የማይችለው ነገር እኔ ከሻለቆቼ ጋር ይምንነጋገርበትን ብቻ ነው። ምክኒያቱም በየወቅቱ ዘመቻ ስንገባ ኣዲስ ኮድ ይዘን ነው የምንገባው። ቀድም ሲል የሠራንበትን ይዘን ኣንገባም። ይህ ከሠንጥቅ ባህርይ ኣንደኛ ብልጫ ነው።

ከዚህ ከፍታ ወደዚህ ከፍታ ሂድ ሲባል ጠላት እየሰማ ለኣለቆቹ ያስተላልፋል። ያዝ የተባልኩት የ3 ቀን ቀለብ ነው። መሬቱ ኣስቸጋሪና ቆላማ ነው። የምንጓዘው ደግሞ እግረ-መንገዳችንን ኣሰሳ እያካሄድን ነው።

ልክ በ3ኛው ቀን ላይ ከጠላት ቃኚዎች ጋር ግጭት ጀመርን። በእነሱ ላይ ጥቂት ጉዳት ኣደርስን። ከእኛም ወገን ቁስለኞች ነበሩ። በ3ኛው ቀን ቀለባችንም ኣለቀ።

ግቡ ወደተባልንበት ኣንድ ጉብታ መሬት (Hill) ላይ ቃኚ ላክንና ከጠላት ጋር ተጋጩ። "እየሸሸን ነው።" የሚል መልእክት የቀዳሚ ሻለቃ ኣዛዥ ኣስተላለፈ። እኔም "እንደጀመርክ 'እየሸሸን ነው'ን ምን ኣመጣው? ይልቅስ ስቦ መግድያ ቦታ እንዳያስገብህ ቀስ ብለህ ረጋ በልና ከከፍታው ሥፍራ ግራና ቀኝ ኣንዳንድ ጓድ ኣውጥተህ መሬቱን ተመልከት።" ኣልኩት።

ወደ ግራም፡ ቀኝም ቃኚ ሲያውጣ ብጉብታማው ላይ ጠላት እሱን ለመክበብ በዝቅተኛው መሬት ውስጥ እየሮጠ መሆኑን ቃኚው ነገረው። ቦታውን ጠላት ጥሩ የመግድያ ቦታ ለማድረግ ኣስቦ ነበር።

10 ሰዓት ገደማ (Around 4 PM) ይሆናል። ምሽቱ እየተጠጋ መጣ። በኣንዳንድ ገዢ መሬቶች ላይ ካሊበር (High caliber weapon) ቢጠምድ በቀላሉ ሊመታን ይችላል። እንደምንከበብ ኣወቅሁ። ትዕዛዝ በሬድዮ ማስተላልፉንም ስለተጠራጠርኩ በተላላኪ ማስተላለፍ ጀመርኩ።

. . . . . . . . . . .

<u>ወደ ክፍል ፪ ይቀጥላል።</u>

# SNAP SHOT

**The following is a time machine report.**

**Melebso, Halal Frontline**
**October 10, 1985**



**Melebso, at the foot of the strategic mountain. Colonel Kasaye Chemeda and his elite Senteq Brigade have quietly slipped "behind enemy line" in this rugged mountain facing Melebso.**

## Today the Ethiopian Army has launched anti-EPLF offensive, whose objective is the capture of Nakfa "within five days."

**High tensions between Ethiopian Army and EPLF occur around the strategic mountain overlooking Melebso.**

**Melebso is a village located in Senhit district of Eritrea. The village is the capital of Maria people, a clan belonging to Bilen nationality that resides in the centre of Eritrea. The village is located 11 kilometres northeast of Halhal.**

**Colonel Kasaye Chemeda and two Shaleqas of the elite brigade, 16TH Senteq Mechanized Brigade have quietly slipped to the rear of EPLF strongholds dug in the strategic mountain overlooking Melebso. An Ethiopian Shaleqa is a battalion consisting 800 -1,000 soldiers.**

**In the early morning of October 10, 1985, the Ethiopian Colonel and his elite Senteq Brigade have placed themselves in collision course against Eritrean Peteros Solomon, director of Military Intelligence and Surveillance of EPLF, in this highly contested strategic mountain of Melebso.**



ግንባር ሰሜናዊ ምብራቕ ሳሕል
ግንባር ናቕፋ
ግንባር ሓልሓል
17
ሣህል
ከረን
MELEBSO
ናቕፋ
ሓልሓል
ቀልመት
ከረን
1:1,000,000

**<u>Continues on Part - 2</u>**

---

**Haile Menegesha Okbe**
**Contact phone: 416-858 9305**
**Email: haileokbe@yahoo.com**